ደንብ ቁጥር----------/2015

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ክፍያን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚጠቀሙበት የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል የህግ ክፍል ማስታወቂያ ደንብ በ1945 ዓ.ም የወጣና ማሻሻያ ሳይደረግበት የቆየ በመሆኑ እንዲሁም በደንቡ ያልተሸፈኑ በርካታ ጉዳዮች በመኖራቸው፤

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አሁን ከደረሱበት ወቅታዊ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና ከሚሰጡት አገልግሎት አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ የዳኝነት ክፍያ ማስከፈል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 55 (1) መሰረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ክፍያ ደንብ ቁጥር ...../2015 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካለሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

1. “አዋጅ“ ማለት የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ማለት ነው፡፡
2. **“ፍርድ ቤቶች”** የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡

Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment

3. **“ ሬጅስትራር”** ማለት በሌላ ሕግ የተሰጠው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በጉባዔ ሹመት ተሰጥቶት የዳኝነት ክፍያውን በበላይነት የሚመራ ነው፡፡
4. **“በገንዘብ የሚተመን ክስ”** ማለት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ ገንዘብን የሚመለከት ወይም ክስ የቀረበበት ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ማናቸውም ንብረት በገንዘብ ሊተመን የሚችል ማለት ነው፡፡
5. **“በገንዘብ ሊተመን የማይችል ክስ”** በባህሪያቸው በገንዘብ ሊገመቱ የማይችሉ ወይም ከግለሰብ ስብዕና ጋር የተያያዙ የመብት ማስከበር አቤቱታዎች ማለት ነው፡፡
6. **“አቤቱታ”** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት ለፍርድ ቤት የቀረበ ክስ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት፣ የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ፣ የሰበር ማመልከቻ፣ ድጋሜ ዳኝነት እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ እና ማናቸውም ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ማለት ነው፡፡
7. **“የዳኝነት ክፍያ”** ማለት ክስ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ፣ የይግባኝ አቤቱታ፣ መስቀለኛ ይግባኝ ወይም መስቀለኛ መቃወሚያ ወይም የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ወገን እንደዚሁም በዚህ ደንብ መሰረት ሊከፈሉ የሚገቡ ማናቸውም ክፍያዎች የሚመለከት ሲሆን በመንግሰት ተቋማት አማካይነት የሚቀርብን ክስ፣ ይግባኝና መስቀለኛ ይግባኝን እና ማናቸውንም አቤቱታዎች የሚጨምር ነው፡፡
8. **“ግምት”** ማለት በዚህ ደንብ በተቀመጠው ታሪፍ መሰረት አንድ የዳኝነት አገልግሎት ለተጠየቀበት ጉዳይ የሚያስፈልገው የክፍያ መጠን ማለት ነው፡፡
9. **“ደሀ”** አግባብ ባለው ህግ መሠረት የዳኝነት ክፍያ መክፍል የማይችል ሰው ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ 22 (1-5) መሰረት በድሃ ደንብ እንዲከራከር የተፈቀደለት ሰው ማለት ነው፡፡

አንቀጽ 3
የጾታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያጠቃልላል፡፡

አንቀጽ 4
የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ ደንብ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

2. ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከእና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በሚቀርቡ የፌዴራል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡

3. የክልል ፍ/ቤቶች በውክልና ሥልጣን በሚመለከቷቸው የፌዴራል ጉዳዮች ላይ ደንቡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

አንቀጽ 5

ዓላማ

ይህ ደንብ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡት አገልግሎት የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መሰረታዊ መብትን በማይጋፋ መልኩ ተመጣጣኝ የሆነ የዳኝነት ክፍያ እንዲያስከፍሉ ማስቻል፤

2) የዳኝነት ክፍያን በማሻሻል ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት ለጎብረተሰቡ በመስጠት የዳኝነት አገልግሎትን ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል፤

3) የዳኝነት ሥርዓቱ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆን፣ የክስ ምክንያት የሌላቸው ማናቸውም ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት እንዳይቀርቡና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ በማድረግ ለዳኝነት ሥራ አካሄድ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማስቻል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የዳኝነት ክፍያ አከፋፈል</u>

አንቀጽ 6

የዳኝነት ክፍያን ስለማስከፈል፣ ስለሚከፈልበት ጊዜና የአከፋፈል ሥርዓት

1. በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ህግ መሠረት ከዳኝነት ክፍያ ነፃ ካልተደረገ በስቀር ማንኛውም አቤቱታውን ለፍርድ ቤት ያቀረበ ወገን የዳኝነት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

2. በደሀ ደንብ እንዲከራከር ከተፈቀደለት ሰዉ በስተቀር በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሬጅስትራሮች አቤቱታ የሚያቀርበዉን ማንኛዉንም ወገን የዳኝነት ክፍያ የማስከፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. የዳኝነት ክፍያ የሚፈጸመው ፍርድ ቤቱ አመቺ ነው ብሎ ባመነበት በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክ በኩል፣ በክሬዲት፣ በዴቢት ካርድ ወይንም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ሊሆን ይችላል፡፡

4. የዳኝነት ክፍያ የሚፈጸመው የፍርድ ቤት መዝገብ ከመከፈቱና ቁጥር ከመሰጠቱ በፊት ነዉ፡ ፡

5. የሚመለከተው የፍርድ ቤት ሰራተኛ ወይም ረጅስትራር በዚህ ደንብ መሰረት የዳኝነት ክፍያ መከፈሉን ሳያረጋግጥ የፍርድ ቤት መዝገብ መክፈት ወይም እንዲከፈት ማድረግ የለበትም።

6. ባለጉዳዮች በኢ-ፋይሊንግ ሥርዓት፣ በድረ-ገጽ ወይም በኢንተርኔት በመጠቀም አቤቱታ ማቅረብ በሚችሉበት ወቅት ክፍያውን በክሬዲት ካርድ፣ በዴቢት ካርድ፣ በኤልክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ወይም አመቺ በሆኑ ሌሎች የክፍያ ዘዴዎች አማካይነት መፈጸም ይችላሉ።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በየደረጃው የሚገኙ ሬጅስትራሮች የዳኝነት የአገልግሎት ክፍያን ሲያስከፍሉ፣ ክስ የቀረበበት ጉዳይ በገንዘብ ሊተመን የሚችል መሆን አለመሆኑን እና ሊከፈል የሚገባውን መጠን በጥንቃቄ በመለየት ክፍያው እንዲፈጸም ለሚመለከተው ሰራተኛ ወዲያውኑ ማስተላለፍ አለባቸው።

8. አቤቱታ አቅራቢው የዳኝነት ክፍያውን በአግባቡ መክፈሉ ሲረጋገጥ እንደክፍያዉ ዘዴ አይነት ተገቢዉ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ወይም አጭር የኤሌክትሮኒክስ መልዕክት እንዲደርሰዉ ይደረጋል።

9. መዝገብ ተከፍቶ የቀረበለት ችሎት በዚህ ደንብ መሰረት መከፈል የሚገባው የዳኝነት ክፍያ መከፈሉን ማረጋገጥ አለበት።

አንቀጽ 7
የዳኝነት ክፍያ መጠን አወሳሰን

የዳኝነት ክፍያ መጠን የሚወሰነው በዚህ ደንብ ላይ በተመለከተው አግባብ የቀረበውን አቤቱታ በመመልከት ደንቡን መሰረት በማድረግ በሚገኝ ተመን ላይ ተመስርቶ ነው።

አንቀጽ 8
በገንዘብ ሊተመኑ የሚችሉ ክሶች

ለፍርድ ቤት የቀረበዉ አቤቱታ በገንዘብ ሊተመን የሚችልን ጉዳይ የሚመለከት ከሆነ በጉዳዩ የገንዘብ መጠን ላይ በመመስረት በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገዉ የዳኝነት ክፍያ ተመን ሠንጠረዥ ላይ በተመለከተው አግባብ በመቶኛ ተሰልቶ የዳኝነት ክፍያዉ መከፈል አለበት።

አንቀጽ 9

በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶች

በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች መሰረት በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ የተለያዩ አቤቱታዎች ለፍርድ ቤት ሲቀርቡ በሚከተለው መሰረት የዳኝነት ክፍያ ይፈጸማል፡-

1. አቤቱታው የቀረበው ለፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡
2. አቤቱታው የቀረበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 1500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡
3. አቤቱታው የቀረበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

አንቀጽ 10

ተጣምረው ስለሚቀርቡ የክስ ምክንያቶች

በአቤቱታ አቅራቢው ከአንድ በላይ የክስ ምክንያቶችን በአንድ ላይ አጣምሮ በሚያቀርብበት ጊዜ ለእያንዳንዱ የክስ ምክንያት አግባብነት ባለዉ የዚህ ደንብ ድንጋጌ መሰረት ተሰልቶ የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡፡

አንቀጽ 11

ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚከፈሉ ክፍያዎች

1. በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ህግ ከዳኝነት ክፍያ ነጻ ከተደረጉ ወገኖች በስተቀር በፍርድ ቤት ለሚሰጡ ማናቸዉም አገልግሎቶች ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡
2. ከዚህ በታች ለተመለከቱት አገልግሎቶች የሚከፈለዉ ክፍያ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

   ሀ. ለተከራካሪ ወገን ወይም ለምስክር መጥሪያ ለማውጣት ለእያንዳንዱ ምስክር ብር 50 (አምሳ ብር) ይከፈላል፡፡

   ለ. የፍርድ ወይም በመዝገብ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውንም የሠነድ ወይም የኤሌክትሮኒክ ሰነድ ግልባጭ ለመውሰድ በገጽ ብር 5 (አምስት ብር) ይከፈላል፡፡

   ሐ. በቤተሰብ ሕግ መሰረት በባልና ሚስት መካከል ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግን ውል በፍርድ ቤት ለማረጋገጥ ለሚቀርብ አቤቱታ ብር 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

መ. በፍ/ቤት ጊዜአዊ የመጠባበቂያ ዕርምጃ ወይም የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ፤ የግልግል ዳኝነት በፍርድ ቤት አማካይነት እንዲሾም፤ በግልግል ዳኝነት የተሰጠ ጊዜያዊ የመጠባበቂያ ዕርምጃ ወይም ሌላ ትዕዛዝ ተፈጻሚ እንዲሆን ለሚቀርብ ማናቸውም አቤቱታ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

ሠ. የግልግል ዳኛ/ዳኞች በሰጡት ትዕዛዝ ላይ እና ሌሎች ከፍርድ ቤት ባለሙያ፣ ከዉርስ አጣሪ ወይም ከሌሎች ባለሙያዎች የፍርድ ቤቱን የማህተም ማረጋገጫ አገልግሎት ለማግኘት ለሚቀርብ አቤቱታ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

ረ. ጊዜው ያለፈበት የይግባኝ ወይም የሰበር ማስፈቀጃ አቤቱታ ለማቀርብ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

3. ከላይ ከተመለከቱት አገልግሎቶች ውጪ ከፍርድ ቤቱ ከተጠየቀ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት አገልግሎቶች ጋር ተመሳሳይ በሆነ ርዕስ ሥር የተመለከተዉ ክፍያ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 12

በክለሳ ወይም በይግባኝ ለሚቀርቡ ጉዳዮች ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

በህግ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት በተለያዩ የአስተዳደር ተቋማት ታይተው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች በፍርድ ቤት በይግባኝ ወይም ቀጥታ ክስ ለሚቀርብ አቤቱታ ከዚህ በታች የተመለከተው ክፍያ ይከፈላል፡፡

1. አቤቱታው በይግባኝ የቀረበው ለፌዴራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡
2. አቤቱታው በይግባኝ የቀረበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡
3. አቤቱታው በይግባኝ የቀረበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበ ከሆነ ብር 3000 (ሶስት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡
4. በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የቀረበው ለፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 1500 (አንድ ሺህ አመስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment

5. በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የቀረበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

6. በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የቀረበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 2500 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

አንቀጽ 13

በክርክር ሂደት ወይም ከውሳኔ በኋላ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች ስለሚከፈል ዳኝነት

አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ወይም በክርክር ሂደት ጣልቃ ለመግባት በቀረበ አቤቱታ ለሚሰጥ አገልግሎት ቀጥሎ የተመለከተው የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፤

1. ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ውሳኔ አስነስቶ ወደ ክርክሩ ለመግባት ለሚቀርብ አቤቱታ ብር 500 (አምስት መቶ) የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡፡
2. ፍርድን ለመቃወም ለሚቀርብ አአቤቱታ መቃወሚያውን ያቀረበው ወገን አስቀድሞ ተከፍሎ በነበረው ክፍያ ልክ የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡፡
3. ፍርድ እንደገና እንዲታይ ለሚቀርብ አቤቱታ አቤቱታውን ያቀረበው ወገን አስቀድሞ የተከፈለውን የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል፡፡
4 በክርክር ሂደት ጣልቃ ለመግባት ለሚቀርብ አቤቱታ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ አመልካቹ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል፡፡
5 ተከሳሽ የሆነ ወገን 3ኛ ወገን በክሱ ውስጥ እንዲገባ አቤቱታ ሲያቀርብ ተከሳሹ 3ኛው ወገን ኃላፊነት አለበት በሚለው የገንዘብ መጠን ልክ ዳኝነት ይከፍላል፡፡

አንቀጽ 14

አቤቱታ ሲሻሻል ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

ከተከራካሪ ወገኖች አንዳቸዉ በክርክር ሂደት ዉስጥ የአቤቱታ ማሻሻል ጥያቄን ጨምሮ በሚያቀርቡት ማመልከቻ ምክንያት የክርክር ሂደቱ ወደኋላ የሚመለስ ከሆነ ፍርድ ቤቱ እንደ ነገሩ ሁኔታ አስቀድሞ ተደረጎ የነበረዉ የክርክር ሂደት የደረሰበትን ደረጃ፣ የፍርድ ቤቱን ጊዜ እና ወጪ ከግምት ዉስጥ በማስገባት አቤቱታ አቅራቢው ተመጣጣኝ የዳኝነት ክፍያ እንዲከፈል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 15

ፍርድ ለማስፈፀም ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

Daniel Fikadu Law Office https://t.me/lawethiopiacomment

ፍርድ ከተፈረደ በኋላ ፍርድ ለማስፈፀም ለሚቀርብ የአፈፃፀም ማመልከቻ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት የዳኝነት ክፍያ ይፈጸማል፤

ሀ/ ፍርድ ያረፈው ከዜሮ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) ይከፈላል።

ለ/ ፍርድ ያረፈው ከብር 100,0001 (አንድ መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ይከፈላል።

ሐ/ ፍርድ ያረፈው ከብር 200,001 (ሁለት መቶ ሺህ አንድ ብር) አስከ 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) ዳኝነት ይከፈላል።

መ/ ፍርድ ያረፈው ከብር 500,001 (አምስት መቶ ሺህ አንድ ብር) አስከ 1,000,000,000 (አንድ ሚሊዮን ብር) ከሆነ ብር 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል።

ሠ/ ፍርድ ያረፈው ከብር 1,000,0001 (አንድ ሚሊዮን አንድ ብር) እስከ ብር 10,000,000 (አሥር ሚሊዮን ብር) ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ዳኝነት ይከፈላል።

ረ/ ፍርድ ያረፈው ከብር 10,000,001 (አሥር ሚሊዮን አንድ ብር) በላይ ከሆነ ብር 3000 (ሶስት ሺህ ብር) ዳኝነት ይከፈላል።

ሰ/ በፍርድ አፋጻጸም ወቅት የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል አቤቱታ ሲቀርብ አቤቱታ አቅራቢው ፍርዱ ሊፈጸምብኝ አይገባም የሚለው ንብረት ወይንም ገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል።

ሸ/ የፍርድ አፈጻጸሙ በገንዘብ ሊተመን የማይችል ጉዳይን የተመለከተ ከሆነ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ይከፈላል።

አንቀጽ 16

በግልግል ዳኝነት እና በሌሎች ተቋማት የተሰጠ ውሳኔን ለማስፈጸም ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

በግልግል ዳኝነት እና በሌሎች የዳኝነት ስልጣን በተሰጣቸው ተቋማት ውሳኔ ያገኘን ጉዳይ ለማስፈጸም የአፈጻጸም ማመልከቻ ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያው በዚህ ደንብ በአንቀጽ 15 ሥር በተደነገገዉ አግባብ ይፈጸማል።

አንቀጽ 17

በውጪ አገር የተሰጠን ፍርድ ለማስፈጸም ስለሚከፍል የዳኝነት ክፍያ

በሕግ አግባብ በውጪ አገር የተሰጠን ፍርድ በፌዴራል ፍርድ ቤት ለማስፈጸም የሚያስችል የሕግ ድጋፍ ኖሮት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያው ከዚህ በላይ በአንቀጽ 14 በተመለከተው አግባብ ይፈጸማል፡፡

አንቀጽ 18

ለይግባኝ ክርክር ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

ይግባኝን በተመለከተ የሚከፈለው ዳኝነት ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፤

1. የሥር ፍርድ ቤት በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ላይ ተመስርቶ ወደ ዋናው ጉዳይ ሳይገባ መዝገቡን የዘጋው ከሆነ በዚህ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሲያቀርብ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ዳኝነት ይከፍላል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲቀርብ በሥር ፍ/ቤት ለዳኝነት የተከፈለው ገንዘብ ግማሹን ይግባኝ ባዩ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት ዳኝነት ከተጠየቀበት ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ከፊሉን ወይንም የተወሰነውን ባለመቀበል በከፊሉ ላይ ውሳኔ ከሰጠና ይህንኑ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታ ከቀረበ ይግባኝ ባዩ ሳይወሰንልኝ ቀርቷል በሚለው ላይ ብቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 ላይ በተመለከተው መሰረት ተሰልቶ የዳኝነት ክፍያውን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
4. የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ረቺ የሆነ ወገን ውሳኔው የሥነ-ሥርዓት ጉደለት አለበት ወይንም በትክክለኛው ጭብጥ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ አይደለም በማለት መስቀለኛ ይግባኝ ወይንም መስቀለኛ መቃወሚያ የሚያቀርብ ወገን ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል፡፡
5. መስቀለኛ ይግባኙ ወይንም መስቀለኛ መቃወሚያው የቀረበው በከፊል ውደቅ የተደረገን የውሳኔ ክፍል ከሆነ የዳኝነት ክፍያው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ በተመለከተው አግባብ ተሰልቶ ይከፈላል፡፡
6. ግምቱ በገንዘብ የማይተመን ክስ፣ በአንቀጽ 12 መሰረት በአስተዳደር አካላት የተሰጠን ውሳኔ በመቃወም በይግባኝ ወይንም በቀጥታ አቤቱታ ለሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ የተሰጠን ውሳኔ በመቃወም ሊሚቀርብ ይግባኝ በሥር ፍርድ ቤት የተከፈለው ክፍያ ግማሹ የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡፡

7. ጊዜአዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ከዋናው ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊባልበት በሚችል የትዕዛዝ ይግባኝ ላይ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡፡
8. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውክልና ሥልጣኑ በቀጥታም ሆነ በይግባኝ የሚያያቸው ጉዳዮች ላይ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 9 (3) እና (4) መሰረት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲቀርብ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ከ1-5 እና 7 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
9. በግልግል ዳኝነት በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያ ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ሊከፈል ይገባ የነበረው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ይከፈላል፡፡
10. በግልግል ዳኝነት በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያው ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ሊከፈል ይገባ የነበረው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ይከፈላል፡፡
11. በግልግል ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ በቀጥታ ለሰበር ችሎት ከቀረበ የዳኝነት ክፍያው በጉዳዩ በገንዘብ መጠን ላይ ተመስርቶ በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 (1) ወይም (2) ላይ መሰረት የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡፡

አንቀጽ 19

በሰበር ለሚታይ ጉዳይ ስለሚከፈል ዳኝነት ክፍያ

1. የሰበር አቤቱታው የቀረበው በገንዘብ በሚተመን ጉዳይ ሆኖ አቤቱታውም የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ከሆነ ለዚህ ፍ/ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ እሩብ (1/4ኛ) ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡
2. የሰበር አቤቱታው የቀረበው በገንዘብ በሚተመን ጉዳይ ሆኖ አቤቱታውም የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ከሆነ ለዚህ ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ እሩብ (1/4ኛ) ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡
3. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 12 ላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ለመጨረሻው ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡

4. ጊዜአዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ከዋናው ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊባልበት በሚችል ትዕዛዝ ላይ ተመስርቶ ከይግባኝ በኋላ የሰበር አቤቱታ ሲቀርብ ለይግባኝ ሰሚው የመጨረሻ ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡
5. በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) (ሀ)፣ (መ) እና (ሠ) በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ለሰበር ችሎት ሲቀርቡ ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ 1-4 የተመለከተው የዳኝነት ክፍያ እንደየአግባብበቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
6. በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) (ሰ) መሰረት በአስተዳደር አካል የአስተዳደር ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሰበር ችሎት በቀጥታ በሚቀርብበት ጊዜ ብር 3000 (ሶስት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ጉዳዮች

አንቀጽ 20

በዳኝነት ክፍያ መጠን ላይ ስለሚፈጠር አለመግባባት

1. የዳኝነት ክፍያን የሚያስፈጽም የፍርድ ቤቱ ባለሙያ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተከትሎ ክፍያውን ማስፈጸም አለበት፡፡
2. በፍርድ ቤት ባለሙያና በባለጉዳዩ መካከል ከዳኝነት ክፍያ ጋር በተያያዘ አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳዩ ኃላፊነት ለተሰጠዉ ሬጅስትራር ለውሳኔ መቅረብ አለበት፡፡
3. ኃላፊነት የተሰጠዉ ሬጅስትራር የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ይህንን ደንብ፣ የፍትሕብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን እና ሌሎችንም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሰረት በማድረግ ተለዋጭ ቀጠሮ ሳይሰጥ በገለልተኛነት ስሜት በዕለቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. በዳኝነት አከፋፈል ረገድ ኃላፊነት የተሰጠዉ ሬጅስትራር የሰጠዉን ውሳኔ በመቃወም ባለጉዳዩ አቤቱታውን ጉዳዩን ለሚያየው ችሎት ማቅረብ ይችላል፡፡
5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ ከፍርድ በኋላ ወደ ይግባኝ ሰሚ ወይም ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ በሥር ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ አግባብ የሆነበትን ምክንያት በመጥቀስ ለይግባኝ ሰሚው ወይንም ለሰበር ችሎት ከሚያቀርበው ቅሬታ ጋር ለችሎቱ ማቅረብ ይችላል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ችሎትም የቀረበውን ቅሬታ

Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment

መርምሮ በሥር ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ በማነስ ወይም በመብለጥ ከሆነ ተስተካክሎ እንዲከፈል ወይም በትርፍነት የተከፈለው እንዲመለስ ትዕዛዝ መሰጠት ይችላል፡ :

አንቀጽ 21

ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ

ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው አግባብ ለከፋዩ ሊመለስ ይችላል፤

1. ከሳሽ የሆነው ወገን የዳኝነት ክፍያውን ፈጽሞ መዝገቡ ቀጠሮ ከመያዙ በፊት ወይም ቀጠሮ እንደተሰጠው መጥሪያው ወጪ ከመሆኑ በፊት ክሱን ለማቋረጥ ቢወስን ለዳኝነት ከከፈለው ገንዘብ ላይ 5 % (አምስት በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ይመለስለታል፡፡
2. ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት መዝገቡን መርምሮ ከሳሹ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መነሻ ምክንያት የለውም ወይም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት መዝገቡን ቢዘጋ ከተከፈለው ዳኝነት ላይ 10% (አሥር በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ለከሳሹ ይመለስለታል፡ :
3. ከክስ መሰማት በፊት ክስ ቢቋረጥ ከተከፈለው ዳኝነት 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ተመላሽ ይደረጋል፡፡
4. ዳኝነት ተከፍሎ የተከፈተ መዝገብ ጉዳዩ በዳኛ ዓማካይነት ለፍርድ ቤት መር አስማሚ ተመርቶ፤ ጉዳዩ በአስማሚ በኩል እልባት ካገኘ ከሳሹ ወይም ይግባኝ ባዩ ለዳኝነት የከፈለው ገንዘብ በፍርድ ቤት መር እማሚነት መመሪያ ላይ በተቀመጠው አግባብ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
5. ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ከክስ መሰማት በፊት በስምምነት (በእርቅ) ቢጨርሱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ በተመለከተው መሰረት ከተከፈለው ዳኝነት ላይ ተቀንሶ ለከሳሹ ይመለሳል፡፡ ተከሳሹም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቦ ከሆነ በዚሁ አግባብ ይፈጸማል፡፡
6. ከሳሹ ከክስ መሰማት በኋላ ክሱን ቢያነሳ የዳኝነት ክፍያው ሙሉ በሙሉ አይመለስም፡፡

አንቀጽ 22

የዳኝነት ክፍያ የማይከፈልባቸው ጉዳዮች

በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ክፍያ አይከፈልም፡፡

1) የቀለብ ክፍያና የልጅ አስተዳደግን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ፤
2) በሴቶች፣ በሕጻናት፣ በአረጋዊያንና እና መሰል የኀብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ የሚቀርብ የወል መሰረታዊ ሰብዓዊ መብታቻቸዉን ለማስከበር በሲቪል ማኅበራት ማካይነት የሚቀርብ ክስ፤
3) በሕግ አግባብ በድሃ ደንብ እንዲከራከር በፍርድ ቤት የተወሰነለት ሰው፤
4) በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክርክር፤
5) አግባብነት ባለዉ ህግ መሰረት አንድ ሰራተኛ በግሉ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲከለስለት ለሚያቀርበዉ አቤቱታ፤

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 23

መመርያ ስለማውጣት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ መመርያ ማውጣት ይችላል።

አንቀጽ 24

የተሻሩ ሕጎች

1. ስለዳኝነት ክፍያ የወጣው ደንብ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/1945 በዚህ ደንብ ተሽሯል።
2. ይህንን ደንብ የሚጻረሩ ማናቸውም አሰራሮች በዚህ ደንብ ተሽረዋል።

አንቀጽ 25

ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ታገሰ ጫፎ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ

Daniel Fikadu Law Office https://t.me/lawethiopiacomment

Daniel Fikadu Law Office

አባሪ

የዳኝነት ክፍያ ተመን ሰንጠረዥ

በደንቡ መሠረት የክፍያ አተማመን ሠንጠረዥ		
የክስ ገንዘብ መጠን (በብር)	የዳኝነት ክፍያ በመቶኛ (%)	የክፍያ ጣርያ (በብር)
(0 – 20,000]	10%	2,000
(20,001 – 40,000]	9%	3,600
(40,001 – 60,000]	8%	4,800
(60,001 – 80,000]	7%	5,600
(80,001 – 100,000]	6%	6,000
(100,001 – 200,000]	5.0%	10,000
(200,001 – 300,000]	4.9%	14,700
(300,001 – 400,000]	4.8%	19,200
(400,001 – 500,000]	4.7%	23,500
(500,001 – 600,000]	4.6%	27,600
(600,001 – 700,000]	4.5%	31,500
(700,001 – 800,000]	4.4%	35,200
(800,001 – 900,000]	4.3%	38,700
(900,001 – 1,000,000]	4.2%	42,000
(1,000,001 – 2,000,000]	4.1%	82,000
(2,000,001 – 3,000,000]	4.0%	120,000
(3.000,001 – 4,000,000]	3.9%	156,000
(4,000,001 – 5,000,000]	3.8%	190,000
(5,000,001 – 6,000,000]	3.7%	222,000
(6,000,001 – 7,000,000]	3.6%	252,000
(7,000,001 – 8,000,000]	3.5%	280,000
(8,000,001 –9,000,000]	3.4%	306,000
(9,000,001 – 10,000,000]	3.3%	330,000
(10,000,001 – 20,000,000]	2.9%	580,000
(20,000,001 –30,000,000]	2.8%	840,000
(30,000,001 – 40,000,000]	2.7%	1,080,000
(40,000,001 – 50,000,000]	2.6%	1,300,000
(50,000,001 – 60,000,000]	2.5%	1,500,000
(60,000,001 – 70,000,000]	2.4%	1,680,000
(70,000,001 – 80,000,000]	2.3%	1,840,000
(80,000,001 – 90,000,000]	2.2%	1,980,000

Daniel Fikadu Law Office

(90,000,001 – 100,000,000]	2.1%	2,100,000
100,000,001 – 200,000,000]	1.9%	3,800,000
(200,000,001 – 300,000,000]	1.8%	5,400,000
(300,000,001 – 400,000,000]	1.7%	6,800,000
(400,000,001 – 500,000,000]	1.6%	8,000,000
(500,000,001 – 600,000,000]	1.5%	9,000,000
(600,000,001- 700,000,000]	1.4%	9,800,000
(700,000,001- 800,000,000]	1.3%	10,400,000
(800,000,001- 900,000,000]	1.2%	10,800,000
(900,000,001-1,000,000,000]	1.1%	11,000,000
ከ1,000,000,001 በላይ	1%	

Daniel Fikadu Law Office

Daniel Fikadu Law Office. https://t.me/lawethiopiacomment

Daniel Fikadu Law Office

Daniel Fikadu Law Office